
# በኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት
## የኢንፎርሜሽንና ኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት
## የሚዘጋጅ ወርሃዊ ዲጂታል መጽሔት

**ጥቅምት /2018 ዓ.ም**




## ማውጫ


የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ—-———————-—1

የፕሮቶኮል ስልጠና ——————————-—1

የተርኪዩ መግባቢያ ስምምነት——————-—2

የፓኪስታን መግባቢያ ስምምነት ————-—2

ተርኪዬ ኢኮኖሚክ ፎረም————-———-—3

ከተርኪዬ ኩባንያ ጋር ውይይት ————-—3

የፕሬዚዳንቱ የአደጋ ስራ አመራር ምርጫ——4

የሻንሺ ኢትዮጵያ ቢዝነስ ፎረም——————4

የኦሮሚያ ንግድ/ዘ/ማ ምክር ቤት ስብሰባ——5

ከአርባምንጭ ቻምበር ጋር ውይይት————-5

ፕሬዚዳንቱ ስለ ነጋዴ ሴቶች ማኅበር————-6

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ቻምበር————6

ዋና ጸሐፊው ከአዘርባጃን አምባሳደር ጋር——7

የሲዳማ ቻምበር ጉባኤ————————7

ዋና ጸሐፊው ከጃፓን ኩባንያ ጋር ውይይት—8

የማኔጅመንት ስብሰባ————————8

ም/ዋና ጸሐፊው በደቡብ አፍሪካ—————9

ብራንዲንግና ማስታወቂያ ስልጠና ———-10

ብራንዲንግ ስልጠና መጠናቀቅ————10

1ኛ ዙር አሰልጣኞች ስልጠና ——————11

የስልጠና መጠናቀቅ————————11

አርባምንጭ ቻምበር ከአዲስ ቻምበር——12

አርባምንጭ ቻምበር ከክልሉ ንግድ ቢሮ—12

አዲስ ቻምበር በሰላም ዙሪያ ውይይት——13

ሰንደቅ አላማ ቀን———————-—14

የሀዘን መግለጫ————————-15

አድራሻ——-—————————17


### የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የዳይሬክተሮች ቦርድ 6ኛ መደበኛ ስብሰባ የምክር





ቤቱን የ2018 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የስራ አፈጻጸም በመገምገም ፤ በቀረቡት የግሉ ሴክተር ወቅታዊ ተግዳሮቶች ላይ በመወያየትና ቀጣይ አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ መጠናቀቁን የምክር ቤቱ ፕሬዚደንት ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር ገልፀዋል ።

**Har'a walgahii idilee 6ffaa Boordii Daayirektaroota Mana Maree Daldalaa fi Waldaalee Sekteraai** Itiyoophiyaa





raawwii hojii mana marichaa kurmaana jalqabaa bara 2018 gamaaggamuun, qormaata yeroo ammaa damee dhuunfaa mudachaa jiru irratti mari'achuun, kallattii gara fuula duraa kaa'uun xumuramuu isaa Prezidaantiin Mana Marichaa Obbo Sabsib Abbaafiraa Abbaajoobir beeksisaniiru.

### ኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የቦርድ አባላትና ለምክር ቤቱ የኮሙኒኬሽንና የቢዝነስ እና አለምአቀፍ ፕሮቶኮል ስልጠና ተሠጠ።





ከኢፌዴሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒሥቴር ጋር በመተባበር የተሠጠው ሥልጠና ምክር ቤቱ የቢዝነስ ዲፕሎማሲ ስራዎችን የሚሠራ በመሆኑ ትልቅ አቅም የሚፈጥር መሆኑ ተመላክቷል።

የምክር ቤቱ ፕሬዚደንት አቶ ሰብስብ አባፊራ አባጆብር በሥልጠናው ላይ እንደገለጹት በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገራት በሚሠሩ የቢዝነስ ዲፕሎማሢ ሥራዎች የፕሮቶኮል አሠራሮችን መከተል ውጤታማ ሥራዎችን ለመሥራት አጋዥ መሆኑን ተናግረዋል።

ሥልጠናውን የሠጡት በኢፌዴሪ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የመንግስት ፕሮቶኮል፣ ሴርሞኒ እና ኮንፍረንስ ዳይሬክተር አቶ እሸቱ ለገሰ ናቸው።ከእንግዳ








አቀባበል ጀምሮ በግንኙነት አግባቦች ተግባራዊ መደረግ ባለባቸው ተግባራት ዙሪያ ሊተገበሩ የሚገባቸው ጉዳዮችም በስልጠናዉ ተዳሠዋል። ለሀገራዊ የንግድና ኢንቨስትመንት መሥፋፋት፣ ለቢዝነስ ግንኙነቶች ማደግ፣ ለፖለቲካዊ፣ ባህላዊና ማህበራዊ ግንኙነት መዳበርና ሀገራዊ ገጽታን ለመገንባት በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገራት የፕሮቶኮል መርሆችን መተግበር በእጅጉ አስፈላጊ መሆኑም በሥልጠናው ላይ ተጠቁሟል።

## የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ከተርኪዬ የንግድና ኢንዱስትሪ ምክር ቤት ጋር በኢትዮጵያና በቱርክ መካከል በንግድ፣ በኢንቨስትመንትና በኢንዱስትሪ ልማት መካከል ያለውን ትብብር ለማጠናከር የሚያስችል የመግባቢያ ሰነድ ተፈራረመ።





ስምምነቱን በተርኪዬ ኢስታንቡል የተፈራረሙት በተርኪዬ የኢፌዲሪ ባለሙሉ ስልጣን አምባሳደር አደም መሀመድ፣ የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት እና ዋና ጸሐፊው በተገኙበት ነው፡፡፡

የመግባቢያ ስምምነቱን ኢትዮጵያን በመወከል የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዝዳንት ሰብሲብ አባፊራ አባጆቢር እና የቱርክ የንግድና ኢንዱስትሪ ምክር ቤት ተወካዮች ተፈራርመዋል።





የኢትዮጵያን የንግድ ግንኙነት ለማስፋት እና የውጭ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት እያደረገ ያለው ጥረት አካል ነው።



ትብብሩ የጋራ ኢኮኖሚ ልማትና የግሉ ሴክተር ትብብርን የሚደግፉ ኤግዚቢሽኖችን እና የኢንቨስትመንት መድረኮችን ለማዘጋጀት ያገለግላል የንግድ ተልዕኮዎችን፣ ተብሏል።

## የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ከፓኪስታን የንግድና ኢንዱሥትሪ ምክር ቤቶች ፌደሬሽን ጋር የመግባቢያ ሥምምነት ተፈራረሙ።







ሥምምነቱ በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለውን የንግድና ኢንቨሥትመንት ትብብር ከማጠናከር ባሻገር ተቋማዊ ግንኙነትን ወደላቀ ደረጃ እንደሚያሣድገው ይጠበቃል።

የመግባቢያ ሥምምነቱን የተፈራረሙት የምክር ቤቱን ፕሬዚዳንት ሰብስብ አባፍራ አባጆብርን በመወከል የንግድና ኢንቨሥትመንት ማሥፋፊያ ዳይሬክተር አቶ መሀመድ ቃሲም እና የፓኪሥታን የንግድና ኢንዱስትሪ ምክር ቤቶች ፌዴሬሽን ሲንየር ምክትል ፕሬዚደንት ሳቁብ ፋያዝ ማጉን ናቸው።



የፓኪስታን የንግድና ልማት ጉባኤ እና የሜድ ኢን ፓኪስታን ኤግዚቢሽን በአዲስ አበባ ሚሊኒየም አዳራሽ እየተካሄደ ነው።

ሥምምነቱም የዚሁ ዝግጅት አካል ሲሆን የፓኪሥታን የንግድና ኢንዱሥትሪ ምክር ቤቶች ፌዴሬሽን ከኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ባለፈ ከፓን አፍሪካን ቻምበር ኦፍ ኮሜርስና ከሌሎች ተቋማት ጋርም የመግባቢያ ሥምምነት ተፈራርሟል።

## የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር የተመራ ልዑክ ቡድን በአፍሪካ ንግድና ኢኮኖሚክ ፎረም ላይ ተሳትፎ አደረገ።






ፕሬዚዳንቱ እንደገለጹት ዛሬ በቱርክ ኢስታንቡል ቱርክዬ ላይ እየተደረገ ያለው ፎረም ላይ ውጤታማ ተሳትፎ እየተደረገ ነው።

The President of the Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations, Sebsibe Abafira Abajobir, is leading a high-level delegation participating in the Africa Trade and Economic Forum.

According to the President, the Forum which is currently taking place in Istanbul, Turkey is being conducted successfully with productive participation from Ethiopian business community.

Har'a, Waltajjii Daldalaa fi Diinagdee Turkii-Afrikaa Turkii Istaanbulitti gaggeeffamaa jiru irratti jila daldalaa Itoophiyaa dursaa jira.







## በፕሬዝዳንት ሰብሲብ አባፊራ አባጆቢር የተመራ የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ልዑካን ከቱርክ-አፍሪካ ቢዝነስና ኢኮኖሚ ፎረም በፊት ከቱርክ ኩባንያ ጋር ተወያይተዋል።







ኩባንያው በማእድን፣ በግንባታ እና በሌሎችም ዘርፎች በኢትዮጵያ ኢንቨስት ለማድረግ ፍላጎት እንዳለው አስታውቀዋል።

## የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር  የኢትዮጵያ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ምክር ቤት አባል ሆነው ተሰየሙ።



በዚህ በክቡር የኢፌድሪ  ጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ አህመድ (ዶ/ር) ተፈርሞ በወጣው ደብዳቤ የተቋቋመው እና በክቡር ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ተመስገን ጥሩነህ ሰብሳቢነት የሚመራው ምክር ቤት፤ በአዋጅ ቁጥር 1386/2017 መሠረት ከኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት በተጨማሪ ከተለያዩ የሚኒስቴር መ/ቤቶች እና ተቋማት የተወጣጡ 42 አባላትን ያቀፈ ነው።

## የቻይና (ሻንሺ) -ኢትዮጵያ ኢኮኖሚክ እና ንግድ ትብብር ጉባኤ በአዲስ አበባ ተካሄደ።










በጉባኤውም የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ እንዳለው መኮንን፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የመካከለኛው ምሥራቅ፣ እስያ እና ፓስፊክ ሀገራት ጉዳዮች ዳይሬክተር ጀነራል አምባሣደር ደዋኖ ከድር፣ የኢንቨሥትመንት ኮሚሽን ኮሚሽነር ዘለቀ ተመሥገን፣ የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የቦር ድ አባላት እና የሁለቱ ሀገራት የቢዝነስ ተቋማት ተወካዮች ተገኝተዋል።






የሁለቱ ሀገራት ንግድና ኢንቨሥትመንት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የመጣ ሲሆን ኢትዮጵያም በቻይና ቤልት እና ሮድ ኢንሼቲቭ፣ በፎካክ እንዲሁም በብሪክስ ያላት ተሣትፎ እያደገ መምጣቱ በጉባኤው ላይ ተጠቁሟል።

ቻይና በኢትዮጵያ በመሠረተ ልማት ግንባታ እና በሌሎች የልማት ሥራዎች ትልቅ አሥተዋጽኦ የምታበረክት ሀገር መሆኗም ነው የተገለጸው።

ኢትዮጵያ ከምትከተለው የሀገር በቀል ኢኮኖሚ አጀንዳ አንጻር እየወሠደቻቸው የማሻሻያ ሥራዎች ለኢንቨሥትመንት ምቹ ሁኔታ እየፈጠረ በመሆኑ የቻይና ኩባንያዎች ትኩረት በተሠጣቸው የማምረቻ ኢንዱሥትሪ፣ በማዕድን፣ በአይሲቲ እና በሌሎችም መሥኮች በኢትዮጵያ ያላቸውን የኢንቨሥትመንት ድርሻ እንዲያሣድጉ የኢንቨስትመንት ኮሚሽን ጥሪ አቅርቧል።

የሻንሺ ግዛት የንግድ ዲፓርትመንት ምክትል ዳይሬክተር ጀነራል ፋን ዋንቹን በበኩላቸው ኢትዮጵያ ያላት ምቹ ጅኦግራፊያዊ መገኛ እንዲሁም የኢትዮጵያ አየር መንገድ ትልቅ የንግድና ኢንቨሥትመንት አጋጣሚ የሚፈጥር በመሆኑ ለሻንሺ ግዛት ኩባንያዎች ትልቅ እድል መሆኑን ገልጸዋል።





**ኦሮሚያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ዛሬ ባካሄደው 13ኛ መደበኛ የቦርድ ስብሰባው የ2018 የበጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የሥራ አፈፃፀም እና የ2017 የኦዲት ሪፖርት መገምገሙን የኢትዮጵያ እና ኦሮሚያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች ፕሬዚደንት ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር ገለፁ።**




በአዲስ አበባ ራዲሰን ብሉ ሆቴል በተካሄደው በዚህ ስብሰባ ፤ በወቅታዊ የንግዱ ማህበረሰብ ተግዳሮቶች ላይ በመወያየትም አቅጣጫ መቀመጡን አክለዋል።




**ኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት አቶ ሰብስብ አባፊራ የአርባ ምንጭ ከተማ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የቦርድ አባላትን በጽህፈት ቤታቸው ተቀብለው አነጋግረዋል።**




የንግድ ምክር ቤቱ የቦርድ አባላት ከፕሬዚዳንቱ ጋር በነበራቸው ውይይት ወደ ፊት ሊሰሩ በሚገባቸው የትብብር ስራዎች እንዲሁም መተግበር ባለባቸው የተሻሉ አሰራሮች ዙሪያ ተነጋግረዋል።

አቶ ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር ምክር ቤቶች ከኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት እንዲሁም የክልል እና የከተማ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች እርስ በርስ ያሏቸውን መልካም ተሞክሮዎች በመለዋወጥና በመተባበር ተሰሚነታቸው ከፍ እንዲል መስራት እንዳለባቸው ገልጸዋል።




በውይይታቸውም የንግዱ ማኅበረሰብ የሚያጋጥሙትን የተለያዩ ችግሮች ከሚመለከታቸው የመንግስት ባለድርሻ አካላት ጋር በመነጋገር መፍታት እንደሚያስፈልግም ተነስቷል።

የአርባ ምንጭ ከተማ እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት አቶ ቦጋለ ቢታኔ በበኩላቸው ምክር ቤቱ ላደረገላቸው ትብብር ያላቸውን ምስጋና ገልጸው ለወደፊትም የምክር ቤቱ ቀጣይነት ያለው ድጋፍ እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል። በውይይቱም የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የቦርድ አባል መጋቢ ስርዓት ቀሲስ ታዬ ለታ እንዲሁም የምክር ቤቱ ዋና ጸሐፊ ዶክተር ቀነኒሳ ለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሰር) ተገኝተዋል።የአርባ ምንጭ ከተማ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የቦርድ አባላትም ለኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ኃላፊዎች የክብር ስጦታ አበርክተዋል።

**የኢትዮጵያ ነጋዴ ሴቶች ማህበር** **በአጭር ጊዜ ውስጥ ያሳየው ትልቅ ተቋማዊ ለውጥና እድገት ለሌሎች ትልቅ ተሞክሮ እና ብርታት የሚሰጥ ከመሆኑ**





**አንጻር በምሳሌነት ሊጠቀስ የሚገባው መሆኑን የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር ገለጹ::**

**የኢትዮጵያ ነጋዴ ሴቶች ማህበር የምስረታውን ግማሽ አመት አጠቃላይ ስራ አፈፃፀም ሪፖርት እና ፋይናሻል ኦዲት ሪፖርት እንዲሁም ወደፊት ስለሚከናወኑ ተግባራት ከንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚንስቴር መስሪያ ቤት ከመጡ ባለሞያዎች ጋር ውይይት ማካሄዳቸው ተጠቅሷል::**

**በውይይቱም በጣም ውጤታማ ግማሽ አመት እንደነበረና ለወደፊትም ከዚህ በላይ ውጤት ለማምጣት አጠናክረን እንቀጥላለን ሲል የኢትዮጵያ ነጋዴ ሴቶች ማህበር የጠቀሰ ሲሆን በቅርቡም ማህበራችን የራሱ ብድር እና ቁጠባ ተቋም ይኖረዋል ብለዋል።**

**የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት ሰብስብ አባፊራ አባጆቢርም ይህንን ውጤታማነት ጠቅሰው ነው ተግባራችሁ ለሁሉም ምሳሌ ይሆናል ያሉት።**

## የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት 1ኛ ዓመት 3ኛ መደበኛ የቦርድ ስብሰባውን በቡታጅራ ከተማ አካሄደ።




**የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት 1ኛ ዓመት 3ኛ መደበኛ የቦርድ ስብሰባውን በዛሬው ዕለት በቡታጅራ ከተማ አካሄዷል።**

የቦርድ ስብሰባው የክልሉ የንግድ ምክር ቤት ፕሬዝዳንት አቶ ሳኒ ሀሰን እና ም/ፕሬዝዳንት አቶ ወንደሰን አርጋው እንዲሁም የቦርድ አባላቱ በተገኙበት ተካሃዷል።

የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤቱ ስብሰባ የ2017 ዓ/ም አመታዊ የስራ ሪፖርት እና የ2018 ዕቅድ በማዳመጥ በመገምገም እና በማፅደቅ እንዲሁም በተለያዩ የምክር ቤቱ አጀንዳዎች ላይ ተወያይቶ ውሳኔዎችን በማስተላለፍ ተጠናቋል ። (የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት)

**የሚዛን አማን ከተማ አስተዳደር የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የ2017 ዓ.ም ጠቅላላ ጉባኤውን አካሄደ ።**





የምክር ቤት ጉባኤውን በንግግር የከፈቱት የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሬዘዳንት አቶ አንተነህ አዲሱ እንዳሉት ያደጉ አገራት አሁን ላሉበት ደረጃ የደረሱት የግሉ ዘርፍ ተገቢውን ሚና እንዲጫወት ምቹ ሁኔታ በመፍጠራቸውና የግሉ ዘርፍም ድምፁ በተገቢ ሁኔታ እንዲሰማ በአንድነት በመቆማቸው ነው ብለዋል።

የአገራችንና የክልላችን የግል ዘርፍ በተናጠል ከመንቀሳቀስ በየደረጃው ባሉት ምክር ቤቶችና ማህበራት በመታቀፍ ሊንቀሳቀሱ ይገባል ያሉት ፕሬዘዳንቱ የንግድና ዘርፍ ማህበሩ የሚመሰረተው በነጋዴው ፈቃደኝነት ላይ ተመስርቶ መሆኑን አብራርተዋል።

የኢኮኖሚ ዋልታ የሆነው ነጋዴው የህብረተሰብ ክፍል ህጋዊ በሆነ መንገድ ብቻ ሸማቹን እያገለገለ መብትና ጥቅሙ ሲጣስበት ጠበቃ የሚቆምለት ተወካይ የንግድና ዘርፍ ማህበር በመሆኑ ሚናው ከፍተኛ ነው ሲሉ አቶ አንተነህ አክለው ገልጸዋል።

የሚዛን አማን ከተማ አስተዳደር ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሬዘዳንት ወ/ሮ አምሳለ ነጋሽ በበኩላቸው የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት መቋቋሙ ዓላማው በንግዱ ማህበረሰብና መንግስት መካከል ድልድይ ሆኖ እንዲያገለግል ለማስቻል ነው ብለዋል።

በመድረኩ የምክር ቤቱ የ2017 በጀት ዓመት እቅድ አፈፃጸም ሪፖርት፣ የ2018 በጀት ዓመት የምክር ቤቱ እቅድና የኦዲት ሪፖርት ቀርቦ ውይይት እየተደረገበት ይገኛል።በጉባኤው የክልሉ ንግድና ኢንቨስትመንት ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊና የገበያ ልማት ዘርፍ ኃላፊ ወ/ሮ አሰገደች ወልደየስ፣ የቤንች ሸኮ ዞን ንግድና ኢንቨስትመንት መምሪያ ኃላፊ አቶ መስፍን ጉብላ፣ የሚዛን አማን ከተማ አስተዳደር ኢንዱስትሪና ንግድ ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ጌታቸው ታቻን ጨምሮ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ከፍተኛ አመራሮችና የምክር ቤት አባላት ተገኝተዋል።(የቤንች ሸካ ዞን የመንግስት ኮሙኒኬሽን)

**ኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ ዶክተር ቀነኒሣ ለሚ ( ተባባሪ ፕሮፌሠር) በኢትዮጵያ ከአዘርባጃን አምባሣደር ሩስላን ናሲቦቭ ጋር ተወያዩ።**





በውይይታቸውም በሁለቱ ሀገራት መካከል ሠላለው የንግድና ኢንቨሥትመንት ልውውጥ እንዲሁም ሠላሉ መልካም አጋጣሚዎች ተነጋግረዋል።

አምባሣደሩ በተለይም ሀገራቸው በአፍሪካ ለሚኖራት የንግድና ኢንቨሥትመንት ኢትዮጵያን ዋነኛ ቀዳሚ መዳረሻ መግቢያ ለማድረግ ተመራጭ መሆኗን ገልጸዋል።

ዋና ጸሐፊው ዶክተር ቀነኒሣ በኢትዮጵያ ሠላለው ምቹ የንግድና ኢንቨሥትመንት ሁኔታ እንዲሁም ምክር ቤቱ እየሠራቸው ባሉ ሀገራዊ የንግድና ኢንቨሥትመንት እንዲሁም የአቅም ግንባታና ሌሎች ሥራዎች ዙሪያ አብራርተውላቸዋል።

የአዘርባጃን የወጭ ንግድና ኢንቨሥትመንት ፕሮሞሽን ኤጀንሲ-አዝፕሮሞ ምክትል ኮሚሽነር ቱራል ሃጂሊ በበኩላቸው የኢትዮጵያ- አዘርባጃን እንዲሁም የአፍሪካ - አዘርባጃን የኢኮኖሚ ፎረም በአዲስ አበባ እንዲካሄድ ፍላጎት እንዳላቸውም አምባሣደሩ አንሥተዋል።





በሁለቱ ሀገራት የንግድ ምክር ቤቶች መካከል ያለውን ግንኙነት ማጠናከር እንደሚገባም ነው በውይይቱ የተጠቆመው።

የአዘርባጃን የወጭ ንግድና ኢንቨሥትመንት ፕሮሞሽን-አዝፕሮሞ ተወካይ ሳቢር ዘይናሊ እንዲሁም የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ምክትል ዋና ጸሐፊ አቶ ጸደቀ ድጋፌን ጨምሮ ሌሎች የሥራ ኃላፊዎች በውይይቱ ላይ ተገኝተዋል።





**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የዳይሬክተሮች ቦርድ ከክልሉ ንግድና ገበያ ልማት ቢሮ ኃላፊዎች ጋር በቅንጅት የተሰሩ ሥራዎችን በመገምገም በቀጣይ ጊዜያት ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ላይ ውይይት አካሄደ።**





የክልሉ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት አቶ ዘሪሁን ቃሚሶ በመክፈቻ ንግግራቸው እስካሁን ከንግድና ገበያ ልማት ቢሮ በጋራ በቅንጅት እየተሰራ መሆኑን በመግለጽ በቀጣይም ይበልጥ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ገልጸዋል።

አክለው ሀገራችን በቅርቡ የተጀመረው AfCFTA የንግዱ ዘርፍ ሰፊ የገበያ እድል እንዲያገኝ መንገድ የከፈተ እና ተወዳዳሪነት እንደዚሁ ይጨምራል ብለዋል: አያይዘውም በቅርቡ የወጣ የገቢ ግብር አዋጅ በተመለከተ እና ተዛማጅ ጉዳዮች ላይ ከሚመለከተው አካል ጋር በጋራ በመሆኑ የግንዛቤ መፈጠር መድረክ እየተካሄደ መሆኑን ገልጸዋል።የሲዳማ ክልል የንግድና ገበያ ልማት ቢሮ ኃላፊዋ ወ/ሮ ሰላማዊት መኩሪያ በበኩላቸው የግሉን ዘርፍ ማጠናከር የመንግሥት ትኩረት አቅጣጫ መሆኑን ገልጸው እስካሁን የተሰራው ስራ በማበረታታት በቀጣይ እየመጣ ያለውን የንግድ ስርዓት ላይ የክልላችን ነጋዴዎች ተወዳዳሪ መሆን እንዲችሉ በቅንጅት መሠራት እንዳለበት ገልጸዋል።የምክር ቤት ዋና ፀሐፊ አቶ ደመቀ ደፋሮ እንደ ጽ/ቤት እየተሰሩ ያሉ ስራዎች በማቅረብ በቀጣይ ከክልሉ የንግድና ገበያ ልማት ቢሮ በጋራ በምንሰራቸው ጉዳዮች ላይ ለውይይት የሚሆን ጽሑፍ በማቅረብ ሰፊ ውይይት በማድረግ የጋራ አቋም በመያዝ ተጠናቋል።

**የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ዴሌይቲ(Deloitte) ከተሰኘዉ የጃፓን የቢዝነስ አማካሪ ድርጅት ጋር በሶላር ኢነርጂ ላይ ከሚሰራዉ TERRA ከሚባል ድርጅት ጋር የኢትዮጵያ ቢዝነሶች በአጋር ሊሰሩ በሚችሉባቸዉ ሁኔታዎች ላይ ተወያይቷል።**





የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ዋና ፀሐፊ ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ የኢትዮጵያ መንግስት ለዉጭ ኢንቨስተሮች ክፍት ካደረጋቸዉ የቢዝነስ ዘርፎች ታዳሽ ኢነርጂ አንዱ መሆኑን ጠቅሶ በሶላር ኢነርጂ ላይ ከሚሰራዉ TERRA የተሰኘ ድርጅት ጋር በዘርፉ የተሰማሩ የኢትዮጵያ ቢዝነሶችን ማስተሳሰር ለአገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርሙ ስኬት አስተዋፅኦ ማድረግ ነዉ ብለዋል።

በDeloitte  አማካሪ ድርጅት የመንግስትና ፐብሊክ ሰርቪስ ከፍተኛ አማካሪ ሂሮኮ ሆዋኪ እና የመሰረተ ልማትና ካፒታል ፕሮጀክቶች ከፍተኛ አማካሪ ኬንታ ሚያሞቶ በበኩላቸዉ የፕሮጀክቱ ዋና ዓላማ ለስደተኞችና አገር ዉስጥ ተፈናቃዮች የስራ ዕድል መፍጠርና የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ መሆኑን አስረድተዉ ይህንን ለማሳካት TERRA ከኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ጋር ለመስራት ፍላጎት እንዳለዉ አረጋግጠዋል።

**የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የስራ አመራር አባላት የምክር ቤቱን የመጀመርያዉን ሩብ ዓመት የስራ አፈፃፀም ግምገማ አካሂደዋል።**





የምክር ቤቱ ዋና ፀሐፊ ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሰር) የምክር ቤቱ የስራ አመራር አበላት በየሩብ ዓመቱ የዕቅድ አፈፃፀማቸዉን የመገምገም ባህል እንዳልነበራቸዉና ከባለፈዉ በጀት ዓመት ጀምሮ ግን የዕቅድ አፈፃፀም በየሩብ ዓመቱ እየገመገሙ በአፈፃፀም ላይ የታዩ ጉድለቶችን ነቅሶ በማዉጣት የቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎችን እያስቀመጡ መሄድ ስለተጀመረ ስራዎችን በታቀዱት መሰረት ለመከወን መቻሉን አስረድተዋል።





በምክትል ዋና ፀሐፊ አቶ ፀደቀ ድጋፌ የተመራው የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት፤ በጆሃንስበርግ ከደቡብ አፍሪካ ንግድ ማኅበራት ምክር ቤቶች ጋር በመተባበር በሁለቱ አገራት መካከል ያለውን የንግድና ኢንቨስትመንት ግንኙነት ለማጠናከር ያለመ





በከፍተኛ ደረጃ ቢዝነስ ለቢዝነስ (B2B) ዉይይት እያደረገ ነው ።

የቢ2ቢ ፎረሙ የገበያ ተደራሽነትን ለማሻሻል፣ የውጭ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ እና የኢትዮጵያን ምርቶች በደቡባዊ አፍሪካ ቀጣና በማስተዋወቅ ላይ ያተኮረ ውይይት በማድረግ ቀጥሏል።

ዝግጅቱ ለንግድ መሪዎች ትስስር፣ የጋራ ስራዎችን ለመመርመር እና ድንበር ተሻጋሪ ንግድን እና ዘላቂ የኢኮኖሚ ትብብርን በሚደግፉ የንግድ ማዕቀፎች ላይ በመወያየት ለንግድ መሪዎች ወሳኝ መድረክ ነው ።

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ልዑክ በደቡብ አፍሪካ የንግድ ጉብኝቱን የሚቀጥል ሲሆን፣ ተልዕኮውም ለሁለቱም አገሮች ፍሬያማ









ውጤት ያስገኛል ተብሎ ይጠበቃል።

**Manni Maree Daldalaa fi Industirii Itiyoophiyaa itti aanaa barreessaa olaanaa isaa Atoo Tsedekeh Degafe tiin durfamu, Mana Maree Daldalaa fi Industirii Afrikaa Kibbaa (SACI) waliin ta'uun waltajjii sadarkaa olaanaa Bizinesii to Bizinesii (B2B) Johaannesbarg keessatti gaggeessaa jira.**

**Waltajjiin B2B kun itti fufee marii qaqqabummaa gabaa fooyyessuu, invastimantii biyya alaa hawwachuu fi oomishaalee Itiyoophiyaa naannoo Gaanfa Afrikaatti beeksisuu irratti xiyyeeffate. Sagantaan kun hoggantoonni daldalaa waltajjii murteessaa walitti hidhami-insa uumuu, walta'iinsa waliinii qorachuu fi bu'uuraalee daldalaa daldala daangaa qaxxaamuraa fi tumsa dinagdee itti fufiinsa qabu deeggaran irratti mari'achuudha.**

**Jilli ECCSA daawwannaa gabaa fi sochii daldalaa Afrikaa Kibbaa keessatti itti fufee yeroo jirutti ergamni kun biyyoota lamaaniif bu'aa bu'a qabeessa akka argamsiisu wal-abdiidha.**





## የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት በብራንዲንግ እና አድቨርታይዝመንት ዘርፍ ለተለያዩ የቢዝነሥ ተቋማት ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ሥልጠና ሠጠ።

ምክር ቤቱ ከሚሠራቸው ዋና ዋና ሥራዎች መካከል የአቅም ግንባታ እና ሥልጠና አንዱ ነው።





ሥልጠናው የሚሠጠው ምክር ቤቱ ከሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር እንዲሁም ከSNV- LIWAY ፕሮጀክት ባገኘው ድጋፍ ነው።

የምክር ቤቱ ምክትል ዋና ጸሐፊ አቶ ጸደቀ ድጋፌ በመክፈቻ ፕሮግራሙ ላይ የኢትዮጵያ ቢዝነሶች በሀገር ውሥጥም ሆነ በአፍሪካና በሌላው ዓለም ዘንድ ተወዳዳሪ መሆን እንዲችሉ ምክር ቤቱ ተከታታይ ሥልጠናዎችን እየሠጠ መሆኑን ገልፀዋል።

በቢዝነስ አመራር አካዳሚ በኩል በዲጂታል ቴክኖሎጅ አጠቃቀም፣ ምርትና አገልግሎትን በማሥተዋወቅ እና በምርትና አገልግሎት ብራንዲግ እንዲሁም በሌሎችም





ዘርፎች ቀጣይነት ያላቸው ሥልጠናዎች እንደሚሠጡም ገልጸዋል። ምክር ቤቱ ከሣምንት በፊት ተከታታይ የአሠልጣኞች ሥልጠና ሲሰጥ መቆየቱ ይታወቃል።

## በብራንዲንግ እና አድቨርታይዝመንት ዘርፍ ለተለያዩ የቢዝነሥ ተቋማት ባለሙያዎች ሲሰጥ የነበረው ሥልጠና ተጠናቀቀ።




የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ቢዝነስ አመራር አካዳሚ ከሥራና ክህሎት ሚኒስቴር እንዲሁም ከSNV- LIWAY ፕሮጀክት ጋር በመተባበር ከ45 በላይ ለሚሆኑ ባለሙያዎች ነበር ሥልጠናው የተሠጠው።

የምክር ቤቱ የቢዝነስ አመራር አካዳሚ ዳይሬክተር አቶ ብሥራት በለጠ በማጠናቀቂያ ፕሮግራሙ ላይ ሥልጠናው ዘመናዊ ቢዝነሥን ለመምራት፣ ለማሥተዋወቅና ተወዳዳሪነትን ለመምጣት ወቅቱ የሚፈልገው መሆኑን ገልጸዋል።



በአካዳሚው በኩል ቀጣይነት ያላቸው ሥልጠናዎች እንደሚሠጡም አቶ ብሥራት ገልጸዋል።

ሠልጣኞችም የተሠጠው ሥልጠና በተግባር የተደገፈ፣ ወቅቱን የጠበቀና ምርትና አገልግሎትን በአግባቡ ለማሥተዋወቅ እንደሚረዳቸው አስተያየታቸውን ሠጥተዋል።

## የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የቢዝነስ የአሠልጣኞች ስልጠና (Training of Trainers) ተጠናቀቀ።

ስልጠናው ምክር ቤቱ ከSNV - LIWAY ፕሮጀክት እንዲሁም ከስራና ክህሎት ሚኑስቴር ጋር በመተባበር ያዘጋጀውና የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ስትራቴጂን ውጤታማ







ለማድረግና የቢዝነስ ተቋማትን አቅም ለመገንባት ያለመ ነው።

በሥልጠናውማጠናቀቂያላይየተገኙት የምክር ቤቱ የኢንፎርሜሽንና ኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ተሾመ ዋቅጅራ





የምክር ቤቱ አንዱ ተልዕኮ ሥልጠናና አቅም ግንባታ መሆኑን በመጠቆም ከትምህርት ተቋማትና ከኢንዱሥትሪው የተውጣጡ ሠፊ እውቀትና ልምድ ያላቸው አሠልጣኞች ለቢዝነስ ከባቢው ትልቅ አቅም እንደሚፈጥሩ ገልጸዋል። የኢትዮጵያ ቢዝነሶች ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪና ዘመናዊ አሠራርን የተከተሉ እንዲሆኑ ሥልጠናው አቅም የሚፈጥር እንደሆነም በሥልጠናው ላይ ተገልጿል። ሥልጠናውን ላጠናቀቁ አሠልጣኞችም ከምክር ቤቱ የማጠናቀቂያ ምሥክር ወረቀት ተበርክቶላቸዋል።

## ሁለተኛው ዙር የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የቢዝነስ የአሠልጣኞች ስልጠና (Training of Trainers) መሰጠት ተጀመረ፣







ስልጠናው ምክር ቤቱ ከSNV - LIWAY ፕሮጀክት እንዲሁም ከስራና ክህሎት ሚኑስቴር ጋር በመተባበር ያዘጋጀው ሲሆን በተለይም የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ስትራቴጂን ውጤታማ ለማድረግና የቢዝነስ ተቋማትን አቅም ለመገንባት ያለመ መሆኑን የምክር ቤቱ የቢዝነስ አመራር አካዳሚ ዳይሬክተር አቶ ብስራት በለጠ ገልጸዋል።





በመሆኑም ሥልጠናው በዲጂታል ማርኬቲንግ፣ በአድቨርታይዝመንት እና ብራንዲንግ እንዲሁም በኢ-ኮሜርስና ሌሎች መሥኮች ላይ ያተኮረ ነው።

ሥራና ክህሎት ሚኒስቴርም የሥልጠና ሞጁሎችን በማዘጋጀት የተሣካና ቀጣይነት ያለው ሥልጠና እንዲሠጥ እየሠራ ይገኛል። ሠልጣኞችም ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትን ጨምሮ ከተለያዩ ድርጅቶች የተውጣጡ አሠልጣኞች ናቸው። SNV የተሠኘው ተቋም በግብርናና ምግብ፣ በኃይል እና በሌሎች መሥኮች የሚሠራ የኔዘርላንድ የልማት ድርጅት ነው።

## የአዲስ ቻምበር የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ከአርባ ምንጭ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር አቻው ጋር አብሮ ለመስራት በሚያስችሉ ጉዳዮች ዙርያ ውጤታማ ውይይት አካሄደ።






በደቡብ ኢትዮጵያ ጠንካራ ከሚባሉ ንግድ ምክር ቤቶች አንዱ የሆነው የአርባ ምንጭ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የቦርድ አመራሮች በአዲስ ቻምበር ዋና መስሪያ ቤት በመገኘት የስራ ጉብኝት እንዲሁም በጋራ ለመስራት በሚያስችሉ ጉዳዮች ዙርያ ጠቃሚ ውይይት አካሄደዋል። በውይይታቸው ወቅት የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት አዲስ ቻምበር የረጅም አመት የስራ ልምድና ተሞክሮ በከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች አማካኝነት ለልኡካ ቡድኑ ገለጻ ተደርጓል።

በውይይታቸው ወቅት የአዲስ ቻምበር ፕረዚደንት ወ/ሮ ዘሀራ መሀመድ ምክር ቤታቸው ከመቼውም ጊዜ በበለጠ የንግዱ ማህበረሰብ ድምጽ ለመሆን በመስራት ላይ እንደሚገኝ የገለጹ ሲሆን ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ከአነስተኛ የንግድ ተቋማት ጀምሮ  እስከ ትላልቅ ኩባንያዎች ድረስ የሚደርስ አገልግሎትን ተደራሽ በማድረግ ላይ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

በተለይም የሀገር ውስጥ የቢዝነስ ተቋማትን ተወዳዳሪ ለማድረግ ምክር ቤታቸው ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ እንደሚገኝ በመግለጽ በተለይም በውጭ ሀገራት ከሚገኙ አቻ የንግድ ምክር ቤቶች እና የንግድ ተቋማት ጋር በቅርበት በመስራት ንግድና ኢንቨስትመንት እንዲያድግ በመስራት ላይ እንደሚገኙ ተናግረዋል። ከዚህም ባለፈ ምክር ቤታቸው የኩባንያ ማህበራዊ ኃላፊነትን ለመወጣት የሚያስችል ስራዎችን በስፋት በመስራት ላይ እንደሚገኝ አክለው ገልጸዋል።



የአዲስ ቻምበር ዋና ጸሀፊ መሰረት ሞላ ( ዶ/ር) በበኩላቸው አዲስ ቻምበር ምቹ የሆነ የንግድና ኢንቨስትመንት ፖሊሲዎች እንዲቀረጹ፤ ተወዳዳሪ የንግድ አውድ እንዲፈጠር፤ የንግድና ኢንቨስትመንት ትስስሮች እንዲዳብሩ የሚያስችሉ የፖሊሲና አድቮኬሲ ስራዎችን ከአጋር አካላት ጋር በመሆን እየሰራ እንደሚገኝ ይህንንም አጠናክሮ እንደሚቀጥል ተናግረዋል።

የአርባ ምንጭ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕረዚደንት ኢንጂነር በጋለ ቤታነህ በበኩላቸው ስለ አዲስ ቻምበር ታሪካዊ አመጣጥና እድገት እንዲሁም ስለ አገልግሎት አሰጣጡ ያገኙት መረጃ ለምክር ቤታቸው ሰፊ ልምድና ተሞክሮን እንዳስገኘላቸው የገለጹ ሲሆን ምክር ቤታቸው ከአዲስ ቻምበር ጋር በጋራ ለመስራት ፍላጎት እንዳላቸው ተናግረዋል። በተለይም የሁለቱ ከተሞች ነጋዴዎችን የሚያጋጥሙ ችግሮችን በጋራ ለመፍታት የሚያስችል ስልታዊ አጋርነት እንዲጠናከር ጥሪ አቅርበዋል።

በሁለቱ ምክር ቤቶች የቦርድ አመራሮች መካከል የተደረገው የልምድ ልውውጥ በቀጣይ አብሮ ለመስራት በሚያስችሉ ስትራቴጂክ ጉዳዮች ላይ ትኩረቱን አድርጓል። የሁለቱ ተቋማት መሪዎች ከውይይታቸው በኋላ የአዲስ ቻምበር ዋና መስሪያ ቤት ህንጻን እና የስራ ክፍሎችን ተዘዋውረው ጎብኝተዋል። (የአዲስ አበባ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት)

## የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የቦርድ አባላት ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ንግድና ገበያ ልማት ቢሮ ኃላፊዎች ጋር በቀጣይ የስራ ግንኙነቶች ላይ ውይይት አካሄዱ::



የምክር ቤቱ የቦርድ አባላት በዛሬው ዕለት ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ንግድና ገበያ ልማት ቢሮ አዳዲስ ኃላፊዎች ጋር የትውውቅ ና የቀጣይ የስራ ግንኙነቶች ላይ ውይይት አካሂደዋል ።

በውይይቱ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ንግድና ገበያ ልማት ቢሮ ኃላፊ ዶ/ር ባዩሽ ተስፋዬ ና ምክትል የቢሮ ኃላፊዎች ከክልሉ የንግድ ና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሬዝዳንት አቶ ሳኒ ሀሰን እና ም/ፕሬዝዳንት አቶ ወንደሰን አርጋው እንዲሁም የቦርድ አባላቱ በተገኙበት  በቀጣይ የቅንጅት ስራ ና ግንኙነት ዙሪያ ሰፋ ያለ ውይይት ተደርጓል ።(የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት)

**አዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የንግድና ኢንቨስትመንት ምህዳር እንዲሻሻልና አባላቱ የሚገጥማቸውን ተግዳሮቶች መፍትሄ እንዲያገኙ የማድረግ ሃላፊነቱን ከሚወጣባቸው መንገዶች መካከል አንዱ በተለያዩ ሀገራዊና የንግድ ጉዳዮች ዙሪያ ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ጋር ምክክር ማድረግ ነው ::**

የዚሁ አንድ አካል የሆነው የምክክር መድረክ 'የንግዱ ማህበረሰብ ሚና ለሰላም ግንባታ ' በሚል ርእሰ ጉዳይ የተካሄደ ሲሆን ንግድና ሰላም ያላቸው ትስስር እና ለሰላም ግንባታ የግሉ ዘርፍ






ያለው ሚና የሚሉ የመነሻ ጽሁፎች ቀርበው ውይይትና ምክክር ተደርጎባቸዋል ።

በምክክር መድረኩ የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር ያደረጉት የአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት/ አዲስ ቻምበር/ ፕሬዚዳንት ወ/ሮ ዘሀራ መሀመድ እንዳሉት ለንግድና ኢንቨስትመንት መስፋፋት ሰላምና መግባባት በጣም አስፈላጊ ጉዳይ መሆኑን ጠቅሰው በሁሉም ቦታ ሰላም እንዲረጋገጥ የንግዱ ህብረተሰብ የሚያደርገውን አስተዋጽኦ ማበርከቱን እንዲቀጥል አሳስበዋል፡ ፡

በሀገሪቱ ያሉ ሁሉም ያገባኛል የሚሉ ወገኖች ይልቁኑም የንግዱ ህብረተሰብ በሀላፊነት ስሜት በሰከነ መንገድ በየደረጃውና በያለበት ተቀራርቦ ለሰላም መስፈን ልዩ ሚና እንዲጫወት ጥሪ አስተላልፈዋል ፡





ንግድ ምክር ቤታቸውም ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ሰላማዊ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴን ለማስቀጠል የግሉ ዘርፍና የመንግስት ትብብር ሚና ከፍተኛ እንደሆነ በመገንዘብ ንግድ ለሰላም በሚል የተዘጋጀው የምክክር መድረክ በንግዱ ህብረተሰብ ዘንድ ሰፊ ግንዛቤን በመፍጠር ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ብለዋል፡ ፤

በመድረኩ ተገኝተው መልእክት ያስተላለፉት የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር ፕሮፌሰር መስፍን አርአያ እንደተናገሩት አንጋፋው የአዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤት እንዲህ አይነቱን ሀገራዊ እና ጠቃሚ የምክክር መድረክ ማዘጋጀቱ እጅጉን የሚያስመሰግነው መሆኑን ጠቅሰው አዲስ ቻምበር የንግዱን ማህበረሰብ ጉዳዮች በተደራጀ ሁኔታ ለሀገራዊ የምክክር ኮሚሽኑ እንዲያቀርብ ጥሪ አቅርበዋል፡ ፤

በመድረኩ የቁልፍ መልእክት ያስተላለፉት የኢትዮጵያ የሃይማኖት ሕብረት ዋና ጸሐፊ ሊቀትጉሃን ቀሲስ ታጋይ ታደለ እንደተናገሩት ሰላም ለሰዎች ብቻ ሳይሆን ለፍጥረታት ሁሉ ከፈጣሪ የተሰጠ ጸጋ ነው ብለዋል።

በሰላም እጦት ሳቢያ ዋነኛ ተጎጂው የንግዱ ህብረተሰብ እንደሆነ ጠቅሰው ዘላቂ ሰላምን በሀገራችን ለማረጋገጥ የሀይማኖት አባቶች፤የአገር ሽማግሌዎች ከንግዱ ሕ/ሰብ በትብብር መሥራት እንዳለባቸው አሳስበዋል።

ዋና ፀሃፊው ቀሲስ ታጋይ አክለውም የአዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤት በንግድና ሰላም ዙሪያ የሚሰራውን መልካም ስራ አጠናክሮ እንዲቀጥል አሳስበው ተቋማቸው ከንግድ ምክር ቤቱ ጋር በዚህ ጉዳይ አብሮ ለመስራት ዝግጁ መሆኑን ጠቅሰዋል ፡ ፡

በመድረኩ ላይ የመነሻና ጥናታዊ ጽሑፎች ቀርበው ውይይት ተደርጎባቸዋል። ' ሰላም በኮርፖሬት ንግድ እይታ' በዶ/ር ጥላሁን በጅቷል ፤ 'ሰላም፤ የህግ የበላይነትና ኢንቨስትመንት በኢትዮጵያ' በአቶ ልኡል ሰገድ ግርማ እንዲሁም 'የንግዱ ማህበረሰብ ሚና ለሰላም ግንባታ' በመጋቢ ታምራት አበጋዝ ቀርቦ ውይይት ተካሂዷል፡ ፤

ውይይቱን ጋዜጠኛ ጥበቡ በለጠ የመራው ሲሆን የአዲስ ቻምብር ዋና ፀሀፊ ዶ/ር መሰረት ሞላ በማጠቃለያ መልእክታቸው የምክክር መድረኩ በልዩ ልዩ የሰላም ነክ ጉዳዮች ላይ የንግዱ ህብረተሰብና መንግስት ተቀራርበው እንዲሰሩ ከማድረጉም በላይ ችግሮች ስር ሳይሰዱ ቶሎ የመቀረፍ እድሉን በማግኘት መፍትሄዎቹንም በጋራ ለማፈላለግ ጠቃሚ ነው ብለዋል፡ ፡

በመድረኩ ላይ የተለያዩ ሀይማኖት አባቶች፤ የሀገር ሽማግሌዎች፤የአዲስ ቻምበር የቦርድና የቀድሞ አመራሮች፤ የምክር ቤቱ የበጎ ፈቃድ አምባሳደሮች፤ታዋቂ ግለሰቦችና ነጋዴዎች፤ የመንግስት ሀላፊዎችና የአጋር ተቋማት ሀላፊዎች ተገኝተዋል፡ ፤

አዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤት በቀጣይም የንግዱን ማህበረሰብ የተመለከቱ ትልልቅ የአድቮኬሲ ጉዳዮች በማንሳት ለምክክር የሚያቀርብ መሆኑ ተጠቁሟል፡ ፤

አዲስ ቻምበር ባላፈው ወርም ከአለም አቀፉ የግል ዘርፍ ኢንተርፕራይዝ ጋር በመተባበር በታክስና ጉምሩክ አሰራሮች ዙሪያ የመንግስትና ግሉ ዘርፍ የምክክር መድረክ ማዘጋጀቱ ይታወቃል።
አዲስ ቻምበር



# እንኳን ለ18ኛው ብሔራዊ የሠንደቅ ዓላማ ቀን አደረሳችሁ!

**“ሠንደቅ ዓላማችን ለኢትዮጵያ ታላቅ የከፍታ ዘመን ብሥራት፣ ለብሔራዊ አንድነታችን፣ ለሉዓላዊነታችንና ለኢትዮጵያ ሕዳሴ”**

## የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት

## የሐዘን መግለጫ

**የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር በአንጋፋው የታሪክ ምሁር ፕሮፌሰር ላጲሶ ጌ. ዴሌቦ ህልፈት የተሰማቸውን ኀዘን ገለፁ።**





**ፕሬዚደንቱ አክለውም ለወዳጅ ዘመዶቻቸው መጽናናትን እንዲሰጥልን እመኛለው ብለዋል።**

# የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት







# የግሉ ዘርፍ ድምጽ!



የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት
Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations
Since 1947

**የንግድ ምክርቤቱ ራዕይ ፣ተልዕኮ ፣ እሴቶች እና ቀዳሚ ስትራቴጂካዊ አምዶች**

## ራዕይ

“በግሉ ዘርፍ የሚመራ ኢኮኖሚና አካታች ዕድገት በሁለት የስትራቴጂክ ዘመናት ውስጥ እውን ሆኖ ማየት”

## ተልዕኮ

“የኢትዮጵያን የግል ዘርፍ በመወከል፣ በመደገፍና ለመብትና ጥቅሙ አድቮኬት በማድረግ፤ ንግድን፣ ኢንቨስትመንትንና ፈጠራን በማስተዋወቅና በማበረታታት አካታች ኢኮኖሚያዊ ዕድገትና ብልፅግናን ማምጣት”

## ዕሴቶች

- _ታማኝነት
- ሙያዊ ብቃት
- አባላት ተኮር ምላሽ ሰጪነት
- ትብብራዊ ጥምረት
- ግልፅነት
- ተጠያቂነት
- ማህበራዊ ኃላፊነት

## ቀዳሚ ስትራቴጂካዊ ጉዳዮች (ስትራቴጂካዊ አምዶች)

1. አድቮኬሲና የፖሊሲ ተፅዕኖ
2. ጠንካራ የአባላት ተሳትፎና ድጋፍ
3. የሀብት ማሰባሰብና በአግባቡ መጠቀም
4. የአቅም ግንባታና ሥርዓት ማሻሻያ
5. ቴክኖሎጂን ማካትት እና ዲጂታል ሽግግር
6. ዘላቂነት ያለው ማኅበራዊ ኃላፊነት
7. ንግድና ኢንቨስትመንት ማስፋፋት
8. ሁሉን-አቀፍ ጉዳዮች (Cross-cutting issues)

**ዋና አዘጋጅ፡-**

ተሾመ ዋቅጂራ

**ም/ዋና አዘጋጅ፡-**

ደበበ አበበ

**አዘጋጅ**

ስማቸው ተበጀ

**ፎቶግራፍ**

ያለምፍሬ በቀለ

**The Ethiopian Chamber of Commerce and Secoral Associations (ECCSA)**

ስልክ: +251115514005
ፋክስ: + 251115517699
P. O. Box 517,
ኢ.ሜይል: info@ethiopianchamber.com
ድረ ገጽ: www.ethiopianchamber.com
ቴሌግራም t.me/ethiopiachamber
ትዊተር https://twitter.com/EthiopiaChamber
ፌስ ቡክ: https://www.facebook.com/EthiopianChamber
Youtube: https://www.youtube.com/channel/UCMEZ4TO8dQiIJvk2IQkTxhA
Linkedin(ሊንክዲን):https://www.linkedin.com/company/ethiopianchamber/in